# <u>ባንዲራችን በሳንዲያጎ !</u>

***በ ቻቻ ማን ያዘዋል***

July 5, 2008 ሳንዲያጎ ካሊፎርኒያ ቅዳሜ … ሱፍ ልብሴን ግጥም አድርጌ ለብሼ አምሮብኝ ተውቤ የትግራይ ልማት ማህበር (TDA) የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽት ዝግጅት አዳራሽ ስገባ ብዙ ሰው አልነበረም፡; በትልቁ ስክሪን ከዚህ በፊት በተላከ ገንዘብ እየተሰራ ያለውን ት/ቤት ህፃናት ሲማሩበት ሳይ ደስ አለኝ፡፡ የ ስድስትና የ ሰባት አመት ህፃናት ልጆች ከአገር ቤት በተኮላተፈ አንደበት " Thank you TDA ካብ ዳስ ናብ ህንፃ" የሚል መፈክር ሲያሰሙ ሳይ ውስጤን ውርር አደረገው፡; የነዚህን ህፃናት እንባ በማበሳቸው ለ ሳንዲያጎዋች እንኳን ደስ ያላችሁ አልኩ በራሴ ግን አፈርኩ መቼ ይሆን እኔም ያቅሜን ያክል እንዲህ አድርጌ አገሬን የምረዳው ብየ አሰብሁ፡፡

ት/ቤቱ ግን መዝጊያ የለውም መስኮትም አልተበጀለትም የሴቶችና የወንዶች ህፃናት ሽንት ቤት በዚያ የሚያልፍ ሰው ከውጭ ሊያየው ይችላል;; የዚህ ምሽት ዝግጅት ታዲያ ይህንን ጅማሮ ከግብ ለማድረስ ነ*ፉ*ል!! እኔ ምናውቄ ጥግ ይዤ የምጠጣውን ይዤ አደይ አብረሀት በነፃ ለዚህ ዝግጅት ብለው ያዘጋጁትን አምባሻ እየገመጥኩ አስተውላለሁ እኔ ቻቻ ማንያዘዋል ታሪክ ሲሰራ እንድመሰክር ተመርጬ ነ*ፉ*ል፡፡

ፕሮግራሙ ተጀመረ፡፡ ሊቀመንበሩ አቶ ልዑል መሓሪ እየመሩት ወ/ሮ አልማዝ እጅግ በሚመስጥ መልኩ ይህንን ት/ቤት እንድንሰራውና እንድናጠናቅቀው ተማፅነው ሲገቡ ሁሉም በውስጡ ተነክቷል፡፡ ዶ/ር ፍሰሃ አገር ቤት በቅርቡ ሄዶ እያለ ያስተዋለውን ምስክርነት ሰጠ ከዚያ

በኋላ ያለውን ግን ካሜራ ካልሆነ ፅሁፍ ይገልጸዋል ብዬ አላምንም። ወጣቱ ባለሱፍ ታዲያ ይህ ነገር አንድ ነገር እናድርግ ብሎ ገና ንግግሩን ሳይጨርስ “እኔ ካሁን በፊት $300.00 ሰጥቼ ነበር አሁን ደግሞ $700.00 እጨምራለሁ” “እኔ $600.00 እጨምራለሁ” “እኔ ካሁን በፊት $1000.00 ሰጥቼ ነበር አሁን ደግሞ $500.00 እጨምራለሁ”... ስድስት ቆነጃጅት ወጣቶች “በመሃላችን 2,100. ዶላር እንሰጣለን” “እኔ ምንም እንኳ በቅርቡ ቢሆንም ስራ ያገኘሁት 100.00 ዶላር እሰጣለሁ”... ያልተጠራ የቁጥር ዓይነት ያልተሰጠ የገንዘብ መጠን አልነበረም። መድረኩ ተናወጠ። ሁለት ወጣቶች እኔ 100.00 ዶላር ብሎ አንዱ ሲናገር ሌላኛው እኔ 300.00 ዶላር ብሎ “ማች”ሲያደርገው በሁለቱ ብቻ $2,900.00 ተዋጣ፡፡ ለአገራቸው ልማት ሲፎካከሩ ማየት ያስቀናል፡፡ ሁለቱ የ ሳንዲያጎ ቻፕተር የ “'ቦርድ አባላት ያደረጉት ፉክክር ደግሞ ሌላኛው  አስደሳች ገጠመኝ ነበር። እኔ 500 ዶላር ሲል ኢንጂነር ጌታቸው እኔ 700.00 ዶላር አለ ፍሰሃ፡ ኢንጂነር 200.00 ዶላር ሲጨምር ፍሰሃ 100.00 ዶላር ሲጨምር ...ሲያልቅ በሁለቱ ብቻ ከ 3,900.00 ዶላር በላይ ተዋጥቷል። አሸናፊው ግን ኢንጂነር ጌታቸው ሆኗል፡፡ ወልደ ግሪማ የጎደለውን እኔ እሞላዋለሁ ሲል አዳራሹ በጭብጨባ ተናጋ። በዚያች አጭር የሁለት ሰአት ቆይታ 15,000 ዶላር ተዋጥቶ ወደ ጭፈራና እልልታ ተገባ። የ 35,000.00 ዶላር ት/ቤት ተጠናቀቀ፡፡

“ዘይገርም” ይላሉ አበው ሲደመሙ ከዚህ የበለጠ ገንዘብ በተዋጣበት ምስክር ሆኛለሁ። “አረደህ” “ከተፊህ” “ወጋህ” “ሰነጠቀህ” እየተባለም ሲዋጣ ማየት የተለመደ ነው ይህኛው ግን ልዩ ነበር።

ሽማግሌዎች ካላቸው ገንዘብ ከራስ በላይ አገር ብለው እስከ 800.00 ዶላር ድረስ የሰጡት እነ ሻምበል ዘኪዎስ; ወጣት ቆነጃጅት ሴቶች ለአገራቸው ሲያበረክቱ; ህፃናት የ አምስትና ስድስት ዓመት ልጆች $1.00 ሲሰጡ (እውነት የትምህርቱ ጉዳይ ገብቷቸው ነው ወይስ "ሃይፕ" ?) ያላቸውን ወረወሩ; መሪዎች በተግባራቸው የሚያስመሰግን ስራ ነው የሰሩት ዘጠኙ የቦርድ አባላት ከ $500-3,000 ድረስ መለገሳቸው ሁሉም ያላቸውን ሰጡ፡; ያልሰጠም አልነበረም!

ፕሮፌሰር መስፍን  በአንድ ወቅት ከቃሊቲ በፃፉት ፅሁፍ ትግሬዎች በአገራቸው ጉዳይ የሚያሳዩት አንድነት አስገራሚ ነው ከሁሉም በፊት ነው ላገራቸው የሚሰለፉት ያሉት እውነት ሁኖ ነው ያገኘሁት፡፡ ብዙዎቹ የረባ ገቢ ስለነበራቸው አልነበረም የሰጡት አለያም የተትረፈረፈ ኑሮ ስላላቸውም አልነበረም የህዝብና የአገር ጉዳይ ስለሆነ እንጂ። እኛ ያገኘነውን እድል ሌላኛው ያገኝ ዘንድ እንጂ በሃብትማ ቢሆን ከነሱ የተሻለ ገቢ ያላቸው ጥሩ ኑሮ የመሰረቱ አሉ። በተግባር የማይገለፅ አገር ማለት አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ በጫማ ማውለብለብ የሚመስላቸው፣ ሌላኛው ጋ ተስማምተው ለመነጋገር ሁሉም ራሱን ጥሎ መምጣት አለበት ብለው ቅድመ ሁኔታ የሚያስቀምጡ፣ የሌላኛውን ህልውና የማይቀበሉ፣ "my way or no way" ብለው የሚሉ፣አገር ሲባል ተራራና ሸንተረሩ እንጂ ህዝቡን የማያዩ፣ ሁሌ ክፉትን ባወሩ ቁጥር ላገራቸው የተቆረቆሩ የሚመስላቸው፣ ሳት ብሎት ስለ አገሩ ጥሩ ነገር የሚያወራን ወያኔ ብለው የሚፈሩ፣ በውይይት መድረክ ባደባባይ አቋም ይዘው ሳይሆን ከ ኢንተርኔት ጀርባ ቋንቋውን ስለቻሉት ብቻ በከባድ ቃላት የሰውን አእምሮ የሚያበላሹ ናቸው፡፡ እናውቃለን የተናገርን እንደሆነ ሁሉም

የሚያውቀውን አንድ ሞኝ ያወጣዋል ብለው እንዳይተርቱብን ፈራን እንጂ እኛማ ለመናገር ፈልገን ነበር።

አገሬ ኢትዮጵያ ውለጅ መንታ መንታውን ያንችን ለቅሶ ማየት የማይሻውን ያለውን ለመስጠት ወደኋላ የማይለውን፤ እያልኩ። በትግሬዎች ግን ኮራሁ። ለአገራቸው ያላቸው ፍቅር ለህዝባቸው ያላቸው ተቆርቋሪነት ውስጤን አተራመሰው ምነው ሁላችንም በነሱ አርአያ አገራችንን ለመርዳት በቻልን ብዬ መንፈሳዊ ቅናት ተሰማኝ።

አባቶቻችን በአክሱም ስልጣኔ የተከሉትን ሃውልት ማስታወሻ የዘመናቸውን ሃውልት ሳንዲያጎዋች በኩሓ መኖስ መንደር ማቆማቸውን ሳይ እንኳን ደስ ያላችሁ። የተከላችሁት ባንድራ ሌላው ይከተለዋል ብዬ መርቄያቸው ተሰናበትኩ። በሌላ ፅሁፌ እስክንገናኝ ቸር ይግጠመን፡፡
07/10/08
ቻቻ ማንያዘዋል
ከሳንዲያጎ